

# ሕግ ምንድነው? በሃገራችን የአፈጻጸሙ ጉዳይ እንዴት ይታያል?

ንዋይ ሃይሉ

መንግስታት በተለዋወጡ ቁጥር የየራሳቸውን ህገ መንግስት አውጥተው በስራ ላይ መዋል ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። በሃገራችን ታሪክም ከፍትሃ ነገስት በኋላ በአጼ ኃይለሥላሴ መንግስት ንጉሱን በማባበልና ለመንግስታቸውም እንዲጠቅማቸው በማስረዳት በንጉሱ መልካም ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የመጀመሪያው ሕገመንግስት በስራ ላይ እንዲውል ተደረገ።በደርግ መንግስትም የሶሻሊስትን ርዕዮተ ዓለም መሰረት በማድረግ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለህዝብ የይስሙላ ውይይት ከቀረበ በኋላ ወደ ሕዝብ ፍላጎት ሳይኬድ ወይም የይስሙላ ውይይት ከተካሄደ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል ተደረገ። የኢህአዴግ መንግስትም ለህዝብ ውይይት ከተላለፈ በኋላ የህዝቡ ማሻሻያዎች ላይ ቀላልና ችግር አያስከትሉም የተባሉትን በማስተካከል ለህዝብና ለሃገር ጠቃሚ የሆኑትን ማሻሻያዎች ባለመቀበል ሕገ መንግስቱ ጸድቆ በስራ ላይ ውሏል።

በሃገራችን ሕገ መንግስት  የሁሉም ህጎች የበላይ በመሆን በስሩ ግን በርካታ ሕጎች ወጥተዋል። ለመጥቀስ ያህል ፣

የፍትሃብሔር ሕግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ የፍትሃ ብሄር ስነስርዓት ሕግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ

ሥነ ስርዓት ሕግ፣ የንግድ ሕግ፣ የባህር ሕግ ወዘተ... ወጥተው በስራ ላይ ውለዋል።

እነዚህ እንግዲህ ለአተረጓጎም ግልጽ በማይሆኑበት ሰዓት ችግር እንዳይከሰት ሕግ አውጪውና ዳኞች እንዲተረጉሙ ሆኖ ይሰራባቸዋል። ሕግ ሲወጣ በአንዲት ሃገር ማንኛውም ግለሰብ በመንግስት ሥርም ሆነ ከመንግስት ውጭ የሚገኙ አካላት ፣ አባላትና መስሪያ ቤቶችም ሊያከብሩት የሚገባ ነው። ከነዚህ ሕጎች በተጨማሪ መስሪያ ቤቶች ከተቋቋሙበት ዓላማ በመነሳት የየራሳቸውን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣሉ። መንግስት አሰሪዎችና ሰራተኞች በጋራ የተስማሙበት አዋጅ (ሕግ) የአሰሪና ሰራተኛ ህግ ይህን መሰረት አድርጎ ደግሞ የህብረት ስምምነት በየደረጃው እየወጡ በስራ ላይ ውለዋል።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት አዋጅም ሆነ የሕብረት ስምምነት በውይይት ወቅት የመንግስት ተወካዮች (የቦርድ አባላት) ጫና በመፍጠርና ቀደም ሲል ከነበራቸው ጠንካራ ይዘት ወርደው በመንግስት ፍላጎት ላይ ብቻ በመመስረታቸው ሰራተኛውን እየጎዱ ይገኛሉ። በአዋጁ ውስጥም ሆነ በህብረት ስምምነት ውስጥ የሰራተኛ መባረር ወይም የሰራተኛ ቅነሳን መሰረት ባላደረገ መልኩ በርካታ ሰራተኞች የሙያ ብቃት ያላቸውና ታታሪ ሰራተኞች ሳይቀሩ ከስራ ተባረው የጫማቸው ሶል እስኪያልቅ እየተንከራተቱ እንዲያውም አንዳንዶቹ በማንኛውም መ/ቤት እንዳይቀጠሩ እየተደረገ ከደህና ኑሮዋቸው ተፈናቅለው ሴቶቹም የዚሁ ሰለባ በመሆናቸው በደህና ጊዜ ያፈሩትን ቤተሰብ (ልጆች) ለመቀለብ በየአስፋልት ላይ በመኪና መንገድ ዳር ተቀምጠው የተለያዩ የአትክልት ምርቶችን ሲሸጡ ሕገወጥ ነጋዴ በመባል በአካባቢ ዘበኛና ፖሊስ በዱላ እየተነረቱ የያዙትን በትነው በመሮጥ ነፍሳቸውን የሚያድኑ ቤቱ ይቁጠራቸው። እዚህ ላይ ሕገ ወጥ ንግድ ይስፋፋ ለማለት ሳይሆን ሰዎች ናቸውና ሰርተው መኖር ስላለባቸው በልቶ ለመኖር መስራት እንዲችሉ ሁኔታዎች ባልተመቻቸበት ለሥቃይ መዳረግ ሕገወጥ ነው፤ ወይም እንደሌሎቹ ሃገሮች በዜግነቱ የሚሰጠው አንድ ሳንቲም እንኳን ሣይኖር እኔ ስበላ ለምን ታየኛለህ ዓይንህ ይጥፋ ብሎ በዱላ አናት መፈርከስ ከምን የመጣ ነው?

በሃገራችን ኢትዮጵያ ለሕግ የተሰጠው ትርጉም በርካታ ነው። በአጠቃላይ ግን ሕግ (ፍትህ) በዜጎች መካከል፣ በግለሰቦች፣ በተለያዩ በግልም ሆነ በመንግስት ተቋማት በሃገር ጉዳይ፣ በሃገሪቱ ሃብት ላይ ምዝበራ፣ ጥቃት፣ በደልና ሕገወጥ ተግባር እንዳይፈጸም ለሁሉም ዜጋ እኩል ማገልገል ያለበት የዳኝነትና የፍትህ ማግኛ ትልቅ መሳሪያ ነው።

ሕግን በየደረጃው አውጥቶ በስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ቢሆንም ዛሬ ወደ ሃገራችን መለስ ብለን ስናስተውል በርካታ ውስብስብ ሁኔታዎች ጎልተው ይታያሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ማንኛውም ፍትህ ሰጪ አካል፣ ግለሰብ(ዳኞች) ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻ ሆነው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የዳኝነት ሥራቸውን ሊሰሩ ይገባል። ዳኞች የሚሾሙት በገዢው መደብ ከሆነ ይነስም ይብዛ ለሾማቸው አካል የመወገን ሁኔታ ሊታይ ይችላል።

አንድ ሃኪም ባለው ሙያ ሰውን የሚያህል የእግዚአብሄር ህንጻ የደረሰበትን በሽታ በመመርመር የተለያየ አካሉን በቀዶ ጥገና መልሶ ጤነኛ ያደርገዋል። ዕውቀቱ የሌለው ሰው በዚህ በኩል ቅደድ ቢለው ሃኪሙ አይቀበልም። የሕግ ሙያም ተመሳሳይነት አለው። ማንኛውም ሰው ጣልቃ ገብቶ በዳኝነት ሥራ ላይ ተጽዕኖ ሳያሳድር በነጻነትና በገለልተኛነት ሊሰሩ ይገባል። በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ፍትህ ለማግኘት በወርና በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሊያልቅ የሚችለው ጉዳይ በልዩ ልዩ የአስፈጻሚ አካላት ምክንያት ማስረጃ ማግኘት እየተቻለ በመደበቅ በተለይ የሰው ምስክሮች ትክክለኛ አድራሻቸው ተረጋግጦ መኖራቸው እየታወቀ እንዲሰወሩና በቀጠሮ ቀን እንዳይገኙ እየተደረገ ለበርካታ አመታት በቀጠሮ እንዲንከራተት የሚደረገውስ ዜጋ ምን ያህል ነው? በአሁኑ ወቅት የሚገኘው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ማንኛውም ሰው እጅ ከፍንጅ ካልተያዘና አጥፊ መሆኑ በፍርድ ቤት ካልተወሰነበት በስተቀር አይታሰርም ይላል፣ ከመንገድ ወይም ከመኖሪያ ቤት ተወስዶ ያለዳኝነት የሚታሰረው ስንቱ ነው? ሌላው በወንጀል የተከሰሰ ሰው ውሳኔ የሚሰጠው የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች መቶ በመቶ ትክክል መሆናቸው ሲታመንበት ብቻ ነው እንደ ፍትሃብሄር ሕግ የሚታየው ማስረጃ  ትክክለኛነቱ የሚያመዝነው የትኛው ነው ወይም የከሳሽ ወይስ የተከሳሽ ተብሎ አይደለም ይህን እንዲሽር ተደርጎ ለላ ሕግ ተቀርጾ ከሆነ አላውቅም። ፍትህ በአፈጻጸም ረገድም ሆነ በዳኝነት ወገንተኝነት ላይ ከተመሰረተ በሕብረተሰብ ላይ ስቃይና ችግር ከማስከተሉም በላይ የአንዲት ሃገር ዕድገትን አስሮ በመያዝ ለበለጠ ውድቀት ሊዳርግ ይችላል። የደርግ መንግስት ባለስልጣናት የሰውን ዘር በማጥፋት ተከሰው ጉዳዩ ለሃገሪቱ ፍርድቤት ቀርቦ ውሳኔ እየተሰጠ ነው። ዛሬስ እየሞተ የሚገኘውን የሰው ልጅ ማነው የሚፈርድለት? ፍርዱንስ የሚያገኘው መቼ ነው? ወይስ እየሞተ እንዲቀር ተወስኖበት ይሆን? ባለፉት መንግስታት የተፈጸመውን ግድያ እያወገዝን ዛሬ ላለው መንግስት ዜጎችን አስፋልት ላይና ሜዳ ላይ እንዲሁም በመኖሪያ ቤታቸው እንዳሉ እንዲገድሉ ማን ስልጣን ሰጣቸው? ታዲያ ህግን ብቻ ሣይሆን እግዚአብሔርንስ አልናቁም ትላላችሁ?

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው አንድ ጊዜ ጉዳዩ ታይቶ ቢወሰንለትም ወይም ቢወሰንበትም እና ጉዳዩ ከተዘጋ ዳግመኛ ክስ ሊመሰረትበት አይችልም ይላል። ለዚህ ይሆን ጉዳዩ ሁለተኛ እንዳይነሳ የገደልኩት በናንተ ምክንያት ነውና ኑ ተጠየቁ የተባለው? የገደለው ቁጭ ብሎ ሌላው ሲጠየቅ ምን ማለት ይሆን? ሕጉ ግን ይህን በግልጽ ይቃወማል።

hailuneway@yahoo.com